# በልማት አጋሮች ድጋፍ ለሚተገበሩ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች የውሎ አበልና ሌሎች ተዛማጅ ወጪዎች የአከፋፈል መመሪያ ቁጥር 1118/2018

ሕዳር 2018 ዓ.ም/ December 2025
የገንዘብ ሚኒስቴር
አዲስ አበባ

Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on the 5th December 202

## መግቢያ

ሀገራችን በአስር አመቱ መሪ የልማት ዕቅድ የተቀመጡ የልማት ግቦችን ለማሳካት ለፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚጠይቀውን ግዙፍ መዋለ-ንዋይ ለማሟላት የሀገር ውስጥ ጥሪትን አሟጦ ከመጠቀም ባሻገር ከልማት አጋሮች የውጭ ሀብት በማሰባሰብና ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ በማድረግ የተለያዩ የረጅምና የአጭር ጊዜ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡ መንግስት ከልማት አጋሮች ጋር ጠንካራ የኢኮኖሚ ትብብር በመመስረቱ የሀገሪቱን የልማት ዕቅዶች ለማሳካት በተለያዩ መስኮች ድጋፍ እየተገኘ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህ አለማቀፍ የኢኮኖሚ ትብብር ሀገራችን በቀጣይ ዓመታት የኢኮኖሚ ዕድገት እንድታስመዘግብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

ባለፉት ዓመታት ሀገራችን ያስመዘገበችውን ሁለገብ ዕድገት ለማስቀጠልና የዜጎችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ሁለተኛው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ፕሮግራም ተቀርጾ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም በማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የተቀመጡትን ግቦች ለማሳካት የተቀረፁ ፕሮጀክቶችን ፋይናንስ ለማድረግ ከሀገር ውስጥ ሀብት በተጨማሪ ከልማት አጋሮች የሚገኘው የውጪ ሀብት ትርጉም ያለው ድርሻ እንደሚይዝ ይታወቃል፡፡

ከልማት አጋሮች በብድርና እርዳታ መልክ የሚገኘው ሀብት በኢኮኖሚው ውስጥ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችሉ መሠረተ ልማቶችን፤ ዘላቂ የልማትና የማህበራዊ አገልግሎት ፕሮግራሞችን እንዲሁም ለዜጎች መሠረታዊ ከለላ ትርጉም ያለው ጠቀሜታ የሚሰጡ እንደ ውሃ፤ ትምህርት፤ ጤና፤ የምግብ ዋስትና እና የመሳሰሉ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶችን ፋይናንስ ለማድረግ የሚውል በመሆኑ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡

የልማት አጋሮች የሚሰጡት የፋይናንስና የቴክኒክ ድጋፍ በትክክል ለታለመለት ዓላማ ስለመዋሉና ተጨባጭ ውጤት ማምጣቱን ለማረጋገጥ በብድር ወይም በእርዳታ ስምምነቱ ውስጥ የአፈጻጸም መከታተያ መለኪያዎች ይካተታሉ፡፡

በዚህም ምክንያት በልማት አጋሮች ድጋፍ በመካሄድ ላይ የሚገኙ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው በጀት፤ ጊዜና ጥራት ተጠናቀው ለዘላቂ ሀገራዊ ልማት መፋጠን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ፤ ከፕሮጀክቶች ቀረፃ ጀምሮ፣ በትግበራ እና ክትትልና ግምገማ ዙሪያ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን መሥራት፤ የማህበረሰብን ተሳትፎ ማረጋገጥ፣ የክትትልና ግምገማ ሥራዎችን ማካሄድ እና ችግሮችን በወቅቱ መፍታት ለፕሮጀክቶች የተሳለጠ አፈጻጸም አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ ባለፈም ሀገራችን ከትብብሩ የምታገኘውን የውጭ ሀብት እንዲጨምር በማድረግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡



የገንዘብ ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት
5

በ2013 ዓ.ም በልማት አጋሮች ድጋፍ ለሚካሄዱ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሚያገለግል የውሎ አበል እና ተዛማጅ ወጪዎች አከፋፈል መመሪያ ተዘጋጅቶ በስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

ሆኖም እስካሁን በሥራ ላይ የቆየው የውሎ አበል መመሪያ ሳይሻሻል የቆየ በመሆኑና አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር ለማጣጣም እንዲሁም በመስክ ክትትልና ግምገማ ሥራዎች ላይ አውንታዊ ተፅዕኖ ለማሳደር መመሪያው እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1.1. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ በልማት አጋሮች ድጋፍ የሚተገበሩ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው በጀት፣ ጊዜና ጥራት እንዲጠናቀቁ ለማድረግ ከፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ቀረፃ፣ ትግበራ እና ክትትልና ግምገማ ጋር በተያያዘ በሚደረጉ ክንውኖች ወቅት የሚያጋጥሙ ወጪዎችን ለመሸፈን የሚያስችል የውሎ አበልና ተዛማጅ ወጪዎች የአከፋፈል ሥርዓት መዘርጋት ነው፡፡

### 1.2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በልማት አጋሮች ድጋፍ ለሚተገበሩ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች የውሎ አበልና ሌሎች ተዛማጅ ወጪዎች የአከፋፈል መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 1.3. ትርጓሜ

ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም፣

1.3.1 **ተሳታፊ፡-** ማለት በልማት አጋሮች ድጋፍ በሚካሄዱ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ቀረጻ፣ አፈጻጸም፣ ክትትልና ግምገማ ጋር በተያያዘ በአገር ውስጥ በሚደረጉ ሥልጠናዎች፣ ዓውደ-ጥናቶች፣ ስብሰባዎች፣ ሴሚናሮች፣ ኮንፍረንሶች፣ የመስክ ክትትልና ግምገማዎች የማህበረሰብ-አቀፍ ንቅናቄዎች ላይ የሚሳተፍ የመንግስት ቋሚና በጊዜያዊነት ተቀጥሮ በመንግስት መ/ቤት ውስጥ የሚያገለግል ማንኛውም ሠራተኛና የሥራ ኃላፊ ነው፡፡

1.3.2 **ሌሎች ባለድርሻ አካላት፡-** ማለት በልማት አጋሮች ድጋፍ ከሚካሄዱ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ጋር በተያየዘ በሚደረጉ ክንውኖች ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ የተጋበዙ የማህበረሰብ አባላት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማህበረሰብ እና የግሉ ዘርፍ ተወካዮች ማለት ነው፡፡



የገንዘብ የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 5

1.3.3 **ውሎ አበል፡-** ማለት የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባወጣው መመሪያ በተሰጠው ትርጉም መሠረት እንደ አግባብነቱ የቀን ውሎ አበልና የውሎ ገባ አበል ማለት ነው፡፡

1.3.4 **የልማት አጋሮች፡-** ማለት ለልማት ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ የፋይናንስና፣ የቴክኒክ እና የዓይነት ድጋፍ በብድር ወይም በዕርዳታ መልክ በመስጠት የመንግስትን የልማት አጀንዳ የሚደግፉ ዓለም ዓቀፍ ተቋማት፣ መንግስታት፣ ቻሪቲዎችና ፋውንዴሽኖች ናቸው፡፡

1.3.5 **ሌሎች ተዛማጅ ወጪዎች፡-** በልማት አጋሮች ከሚደገፉ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ቀረፃ ክትትልና ግምገማ እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ ክንውኖች ጋር በተያያዘ ከውሎ አበል ውጭ ያሉ የትራንስፖርት ወጪዎች ማለት ነው፡፡

1.3.6 **በልማት አጋሮች ድጋፍ በሚካሄዱ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ላይ የሚካሄዱ ክንውኖች ማለት** በልማት አጋሮች ከሚደገፉ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ቀረፃ፣ አፈጻጸም፣ ክትትልና ግምገማ ጋር በተያያዘ በፌዴራል፣ በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ እና በቀበሌ ደረጃ የሚካሄዱ ስብሰባዎች፣ ሥልጠናዎች፣ ዓውደ-ጥናቶች፣ ሴሚናሮች፣ ኮንፈረንሶች፣ የመስክ ጉብኝቶች፣ ክትትልና ግምገማዎች እና የማህበረሰብ አቀፍ ንቅናቄ ሥራዎች ናቸው፡፡

## 1.4. አውጭው ባለስልጣን

የገንዘብ ሚኒስቴር የውጭ ሀብትን የማሰባሰብና የተሰበሰበው ሀብት በታለመለት መንገድ ተግባራዊ መሆኑን እንዲከታተል በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 1.5. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በልማት አጋሮች ድጋፍ በሚተገበሩ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ በፌደራል፣ በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ እና በቀበሌ በሚዘጋጁ ስብሰባዎች፣ ሴሚናሮች፣ ኮንፍረንሶች፣ ዓውደ-ጥናቶች፣ ስልጠናዎች፣ የመስክ ክትትልና ግምገማዎች፣ የማህበረሰብ-አቀፍ ንቅናቄዎች እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ ስራዎች ሲዘጋጁ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የውሎ አበል

## 2.1 የውሎ አበል አከፋፈል

የውሎ አበል አከፋፈል በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የቀን ውሎ አበል ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 1111/2018 አንቀፅ 6 ተራ ቁጥር 1 መሰረት ለቁርስ 10% ለምሳ 25%፤ ለእራት 25%፤ እንዲሁም ለመኝታ 40% በሚል ተከፋፍሎ የሚሰላ ይሆናል፡፡

የገንዘብ የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 5 ሚኒስቴር

## 2.2 ለውሎ አበል ብቁ የሚያደርጉ ሁኔታዎች

2.2.1. በልማት አጋሮች ድጋፍ በሚካሄዱ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች የተለያዩ ክንውኖች ጋር በተያያዘ ለመስክ ሥራ ተሰማርቶ ዕለቱን ወደ መኖሪያው መመለስ ካልቻለ ለእያንዳንዱ በመስክ ሥራ ለቆየበት ቀን የውሎ አበል የሚከፈለው ይሆናል፡፡

2.2.2. ሆኖም ቀኑን ሙሉ ከሥራ ቦታው ውጭ በመስክ ስራ ላይ አሳልፎ ዕለቱን ወደ መኖሪያው ከተመለሰ የምግብ ወጪውን ለመሸፈን በዚህ መመሪያ ከተራ ቁጥር 2.3.1 እስከ 2.3.4 ድረስ ለቦታው ከተቀመጠው የውሎ አበል ላይ በሲቪል ሰርቪስ መመሪያ አንቀፅ 6 ተራ ቁጥር 1 መሰረት ለምግብ ለሚያወጣው ወጪ ተሰልቶ ይከፈለዋል፡፡

## 2.3 ለመንግስት ሠራተኞች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተግባራዊ የሚሆን የውሎ አበል አከፋፈል

2.3.1 የመንግሥት ሠራተኞች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በአዲስ አበባ ከተማ በሚደረጉ ክንውኖች ላይ ሲሳተፉ ደመወዝን እና የሥራ ደረጃን መሠረት በማድረግ ልዩነት ሳይደረግ በቀን ብር 2,534.00 የውሎ አበል ይከፈላል፡፡

2.3.2 የመንግሥት ሠራተኞች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በክልል ከተሞች (የብዝሀ ከተማ መርህ የሚከተሉ ክልሎች ዋና ከተሞችን ጨምሮ) በሚደረጉ ክንውኖች ላይ ሲሳተፉ ደመወዝን እና የሥራ ደረጃን መሰረት በማድረግ ልዩነት ሳይደረግ በቀን ብር 1,670.00 የውሎ አበል ይከፈላል፡፡

2.3.3 የመንግሥት ሠራተኞች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በዞን ከተሞች በሚደረጉ ክንውኖች ላይ ሲሳተፉ ደመወዝን እና የሥራ ደረጃን መሰረት በማድረግ ልዩነት ሳይደረግ በቀን ብር 1,460.00 የውሎ አበል ይከፈላል፡፡

2.3.4 የመንግሥት ሠራተኞች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በወረዳ ዋና ከተሞች ላይ ለሚደረጉ ክንውኖች ላይ ሲሳተፉ ደመወዝን እና የሥራ ደረጃን መሰረት በማድረግ ልዩነት ሳይደረግ በቀን ብር 1,271.00 ይከፈላል፡፡

2.3.5 የመንግሥት ሠራተኞች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በሚኖሩበት ወረዳ ውስጥ በሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች በሚካሄዱ ክንውኖች ላይ ሲሳተፉ ደመወዝን እና የሥራ ደረጃን መሰረት በማድረግ ልዩነት ሳይደረግ ብር 200.00 የውሎ አበል ይከፈላል፡፡

## 2.4 የውሎ አበል የሚከፈልባቸው ቀናት

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ወይም ሌሎች የባለድርሻ አካላት ተሳታፊ ከሥራ ቦታ ውጭ በፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ክንውኖች ላይ ለተሳተፉባቸው/ለቆዩባቸው ቀናት አሁን በስራ ላይ ባለው የሲቪል ሰርቪስ የውሎ አበል አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 8 ተራ ቁጥር 1 በተገለፀው መሰረት የውሎ



የገንዘብ
የሪከርድ
አስተዳደር
አገልግሎት
5
ሚኒስቴር

አበል ይከፈለዋል። በተጨማሪም ከኩነቱ በፊት እና ኩነቱ ካለቀ በኋላ በጉዞ ለሚያሳልፋቸው ቀናት በዚህ መመሪያ ተራ ቁጥር 2.2 መሰረት ተሰልቶ በውሎ አበሉ ላይ ተጨምሮ የሚከፈል ይሆናል።

## 2.5 በአዘጋጆች የተሟላ አገልግሎት ሲሰጥ

ክንውኑን በሚያዘጋጀው ተቋም ወይም መ/ቤት በኩል ለተሳታፊዎች የተሟላ አገልግሎት ማለትም መኝታ፣ ቁርስ፣ ምሳ እና እራት የሚቀርብ ከሆነ ተሳታፊዎች ለሚሳተፉባቸው ቀናት የውሎ አበል አይታሰብላቸውም። ሆኖም ከኩነቱ በፊት እና ኩነቱ ካለቀ በኋላ በጉዞ ለሚያሳልፋቸው ቀናት በዚህ መመሪያ ተራ ቁጥር 2.2 መሰረት ተሰልቶ የውሎ አበል የሚከፈል ይሆናል።

## 2.6 የአየር ፀባይ አበል

ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ እና ባለድርሻ አካል ለሥራ ጉዳይ የአየር ጸባይ አበል ወደ ሚከፈልበት የሥራ ቦታ ሲላክ:-

1. በአንደኛ ደረጃ 40% የአየር ጸባይ አበል ወደሚከፈልበት የሥራ ቦታ የተመደበ ከሆና የቀን ውሎ አበሉ 40% በተጨማሪነት ተሰልቶ ይከፈለዋል።

2. በሁለተኛ ደረጃ 30% የአየር ጸባይ አበል ወደሚከፈልበት የሥራ ቦታ የተመደበ ከሆና የቀን ውሎ አበሉ 30% በተጨማሪነት ተሰልቶ ይከፈለዋል።

3. በሶስተኛ ደረጃ 20% የአየር ጸባይ አበል ወደሚከፈልበት የሥራ ቦታ የተመደበ ከሆና የቀን ውሎ አበሉ 20% በተጨማሪነት ተሰልቶ ይከፈለዋል።

# ክፍል ሶስት
# የትራንስፖርት ወጪ

የሚከተሉትን መረጃዎች መሰረት በማድረግ የትራንስፖርት ወጪዎች የሚወራረዱ ይሆናል።

3.1. አግባብነት ባለው የመንግስት አካል በወጣ የዋጋ ታሪፍ መሰረት ለሚሰጡ የትራንስፖርት አገልግሎቶች በሚቀርብ ህጋዊ ደረሰኝ፤
3.2. በአየር እና በምድር ባቡር ትራንስፖርት የደርሶ መልስ ጉዞ በሚቀርብ ህጋዊ ደረሰኝ፤
3.3. በመስሪያ ቤት ተሽከርካሪ ለሚደረግ ጉዞ ተሽከርካሪው በአማካኝ በሊትር 5 ኪሎ ሜትር ሊጓዝ እንደሚችል ታሳቢ ተደርጎ በሚቀርብ የወቅቱ የነዳጅ ዋጋ ህጋዊ ደረሰኝ፤
3.4. በአየር ትራንስፖርት ለሚደረግ ጉዞ በመ/ቤት የትራንስፖርት አገልግሎት ካልቀረበ ከመኖሪያ ቤት/ሥራ ቦታ ወደ አውሮፕላን ማረፊያ፣ ከአውሮፕላን ማረፊያ ወደ መኖሪያ ቤት/ሥራ ቦታ ለሚደረግ ለእያንዳንዱ ነጠላ ጉዞ የታክሲ ኮንትራት ወጪ መሸፈኛ ብር 550 የሚከፈል ይሆናል።



የገንዘብ
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት
5
ሚኒስቴር

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ

### 4.1. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በሚንስትሩ ከፀደቀበት ከህዳር 01 ቀን 2018 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

### 4.2. የተሻሩ መመሪያዎች

ከዚህ በፊት ከጥቅምት 23 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ላይ ያለው በልማት አጋሮች ድጋፍ ለሚተገበሩ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች የውሎ አበልና ሌሎች ተዛማጅ ወጪዎች የአከፋፈል አፈጻጸም መመሪያ ተሽሯል፡፡

### 4.3. መመሪያን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ በገንዘብ ሚኒስቴር የበላይ መሪነት በየሁለት ዓመቱ የሚከለስና የሚሻሻል ይሆናል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሁለት ዓመት በፊት ወይም ዘግይቶ ሊሻሻል ይችላል::

አህመድ ሺዴ
የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር